መልእክት ስድስት

**በዳዊት ታሪክ ውስጥ የታዩ**
**መንፈሳዊ መርሆች፣ የሕይወት ትምህርቶች፣ እና ቅዱስ ማስጠንቀቂያዎች**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ:- 1 ሳሙ. 16፡1—2 ሳሙ. 24፡25፤ ሐዋ. 13፡22፤ 36

1. **በዳዊት ታሪክ ውስጥ (1 ሳሙ. 16፡1—2 ሳሙ. 24፡25)፣ የእግዚአብሔርን ሉአላዊነት እና ዳዊት የመስቀሉን ትምህርት መማሩን ማየት ያስፈልገናል፡-**

   ሀ. በእግዚአብሔር ሉአላዊነት ሥር ዳዊት እግዚአብሔርን በመታመኑ እና ጎልያድን በማሸነፉ ተፈትኖ ብቁ ሆኖአል—1 ሳሙ. 17፡1-58፡-

      1. ዳዊት እንደ እረኛ የነበረው ልምምድ በጌታ ላይ እንዲታመን አሰልጠኖታል፣ ስለዚህም የጎልያድን መገዳደር ሲሰማ፣ ለሳኦል "እኔ ባሪያህ የአባቴን በጎች ስጠብቅ አንበሳና ድብ ይመጣ ነበር፥ ከመንጋውም ጠቦት ይወስድ ነበር። በኋላውም እከተለውና እመታው ነበር፥ ከአፉም አስጥለው ነበር፤ በተነሣብኝም ጊዜ ጕሮሮውን ይዤ እመታውና እገድለው ነበር። እኔ ባሪያህ አንበሳና ድብ መታሁ፤ ይህም ያልተገረዘው ፍልስጥኤማዊ የሕያውን አምላክ ጭፍሮች ተገዳድሮአልና ከእነርሱ እንደ አንዱ ይሆናል" ማለት ችሏል—ቁ. 34-37።
      2. ዳዊት ለጎልያድ "... እግዚአብሔር በሰይፍና በጦር የሚያድን እንዳይደል ያውቅ ዘንድ ነው። ሰልፉ ለእግዚአብሔር ነውና፤ እናንተንም በእጃችን አሳልፎ ይሰጣል" (ቁ. 47) አለው፤ ዳዊትም ጎልያድን ሊወጋ ሄደ (ቁ. 40-48) ወደ ግንባሩ ውስጥ ጠጠርን አስወንጭፎ በገዛ ሰይፉ ራሱን ቆርጦ ገደለው (ቁ. 49-54)።
      3. ዳዊት በጎልያድ ላይ የተቀዳጀው ድል እግዚአብሔር እርሱን የመምረጡ እና የመቀባቱ ጠንካራ ማረጋገጫ ነበር፤ ዛሬ ክርስቶስን እየተከታተልን ስለሆነ፣ የከባቢ ሁኔታችን እያንዳንዱ ገጽታ ፍጹም በእግዚአብሔር ሉአላዊ እጅ ሥር እንደሆነ ከዳዊት ልምምድ መገንዘብ ያስፈልገናል—ማቴ. 10፡29-31፤ መዝ. 31፡14-15፤ 39፡9፤ ሮሜ. 8፡28-29፤ ኢሳ. 45፡15።

   ለ. በእግዚአብሔር ሉአላዊነት ሥር ዳዊት የጊዜው ንጉሥ የነበረው የሳኦል አገልጋይ እንዲሆን ተመረጠ፣ እነዚህ ሁለቱ በአንድ ላይ በመቀመጣቸው፣ ሳኦል ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር ተቃራኒ የሆነ ሰው እንደሆነ ሲጋለጥ ዳዊት ደግሞ በእግዚአብሔር ልብ መሠረት የሆነ ሰው መሆኑ ተገልጦአል—1 ሳሙ. 18፡6-11፡-

      1. ዳዊት ከሳኦል ጋር ባለው ግንኙነቱ መፈተኑ ዳዊት ባለማቋረጥ ሲሰቀል ነበር ማለት ነው፤ ሳኦል በላከው በእያንዳንዱ ተልእኮ ዳዊት በብልሀት ተንቀሳቀሰ፣ ስለዚህም ሳኦል በጦረኞች ላይ ሾመው፤ አንድ ጊዜ ዳዊት ፍልስጤማውያንን መትቶ ሲመለስ፣ ሴቶቹ ከእስራኤል ከተሞች ሁሉ መጡ፣ አንዳቸው ለሌላቸው—"ሳኦል ሺህ ገደለ፤ ዳዊት ግን እልፍ ገደለ" እያሉ ዘፈኑ—ቁ. 5-7።
      2. ይህ ውዳሴ ዳዊት ላይ ተጽእኖ አላደረገበትም፣ ሳኦል ላይ ግን ተጽእኖ ነበረው፤ ሰሎሞን እንዲህ አለ፣ "ሰውም በሚያመሰግኑት ሰዎች አፍ ይፈተናል" (ምሳ. 27፡21)፤ ሳኦል ሙሉ በሙሉ በሥጋ የሆነ ሰው እንደሆነ እና ለራሱ እንደሆነ በማሳየት እጅግ ተናደደ በዳዊትም ላይ ቀናበት፤ ከዚያ ቀን አንሥቶ ሳኦል ዳዊትን ለመግደል ወሰነ፣ ዳዊትም የሚሸሸግበት ስፍራ አልነበረውም፤ ሳኦል በዳዊት ላይ ከመቅናትም ብሶ የራሱን ስም ሳያበላሽ እንዴት እንዲገድለው ያደባ ጀመር—1 ሳሙ. 18፡10—20፡42።
      3. ሳኦል ሊገድለው ሲሞክር፣ ዳዊት በአጸፋው አልወጋውም ወይም ለመበቀል ምንም አላደረገም፣ ያደረገው መሸሸ ነበር፤ መበቀል እና በአጸፋው መዋጋት የሥጋ ነገሮች ናቸው፣ የሥጋንም ነገር የሚለማመዱ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ እድል ፈንታ የላቸውም—18፡11፤ ተዛ. ሮሜ. 12፡19፤ ኤፌ. 4፡26፤ ገላ. 5፡21፣ 24።
      4. ዳዊት የእግዚአብሔርን ሥልጣን ከልቡ የሚያውቅ ሰው ነበረ፤ በ 1ኛ ሳሙኤል ሳኦል ዳዊትን ሊገድለው በምድረበዳ ሲያሳድደው እንደነበር እናያለን፤ ዳዊት ሳኦልን ሊገድል የሚችልበት እድል ነበረው፣ ነገር ግን እግዚአብሔርን ፈራ እንዲሁም በእግዚአብሔር የተዘጋጀውን መለኮታዊ ሥርዓት ለመገልበጥ አልደፈረም—18፡6—26፡25።
      5. ዳዊት በሳኦል ላይ አምፆ ቢሆን ኖሮ፣ ለሕዝቡ እግዚአብሔር በወሰነው እና በቀባው ንጉሥ ላይ የማመጽ ምሳሌ ይሆን ነበር፤ የዳዊት አመለካከት ራስን የመካድ እና ለእግዚአብሔር ሥልጣን የመገዛት ነበር።
      6. ሳኦል እግዚአብሔርን አልታዘዘም፣ በእግዚአብሔር ተቀባይነት ያጣ ነበር፣ ይህ ግን በሳኦል እና በእግዚአብሔር መካከል ያለ ነገር ነበር፣ ዳዊትን በተመለከተ፣ እግዚአብሔር ለቀባው ተገዛ፣ ይህም በእግዚአብሔር ፊት ኃላፊነቱ ነበር—24፡4-6፤ 26፡9፣ 11፤ 2 ሳሙ. 1፡9-16።

7. አንዳንዶች ከመስቀሉ ሥር በመኖር የመስቀሉን መስበር ለመለማመድ ዋጋ ቢከፍሉ፣ የተፈጥሮአዊ ሰዋቸውን እና ባህሪያቸውን ቢያውቁ እና ቢያድቡ፣ ሥጋን ቢገድሉ እና በእግዚአብሔር ፊት ራሳቸውን ቢክዱ፣ በእርግጠኛነት የእግዚአብሔርን ሥልጣን ያውቃሉ የእግዚአብሔርንም ሥልጣን ማምጣት ይችላሉ—ይህ መሠረታዊ መርህ ነው።
8. በአዲስ ኪዳን ግንዛቤ መሠረት፣ ዳዊት በእያንዳንዱ ቀን በየትኛውም አይነት ሁኔታ መስቀሉን ተሸከመ፤ ፊልጵስዩስ 3፡10 መስቀሉን የምንሸከምበት ጥንካሬ የክርስቶስ የትንሣኤው ኃይል መሆኑን ያመለክታል፤ ክርስቶስ በእኛ ውስጥ ለመኖር እና በውስጣችን መስቀሉን ለመሸከም ወደ ውስጣችን መጥቶአል—ተዛ. መኃ. 2፡8-9፣ 14።
9. ዳዊት የመስቀሉን ትምህርት እየተማረ ሳለ፣ ከዮናታን እና ከሜልኮል ጋር የእግዚአብሔርን አቅርቦት ተደሰተ፤ ያለ እነርሱ ከሳኦል የሚያመልጥበት መንገድ አይኖረውም ነበር—1 ሳሙ. 20፡1-42፤ 19፡11-18።
10. በእግዚአብሔር ሉአላዊነት ሥር ዳዊት የመስቀሉን ትምህርቶች ተማረ፣ በስተመጨረሻም ከሳሪ ሳይሆን አትራፊ እና አሸናፊ፣ መከራን ተቀባይ ሳይሆን ተደሳች ሆነ—ፊልጵ. 1፡19፤ 3፡8-9፤ 2 ቆሮ. 4፡7፣ 16-18፤ ተዛ. 2፡12-14።
11. የዳዊት ሕይወት የመሰበርን ሕይወት ያመለክታል፤ የውጪው ሰው መሰበር የተፈጥሮአዊ ሰዋችን፣ የእኔነታችን መሰበር ነው፤ የመንፈስ ቅዱስ ቅጣት ግቡ የተሰበርን ሰዎች እንድንሆን ነው፤ እግዚአብሔር ፍሊጋ ከሌላቸው ብልጥግናዎቹ ሁሉ ጋር ራሱን ወደውስጣችን የሚያድልበት ነጻ መንገድ ማግኘት ይችል ዘንድ በፍጹም ምንም ማድረግ በማንችልበት እና እርዳታቢስ በምንሆንበት ስፍራ ያስቀምጠናል—1፡8-9፤ 4፡16-18፤ 12፡9-10፤ ሆሴ. 6፡1-3፤ ሮሜ 8፡28-29፤ ተዛ. ዮሐ. 12፡3።

**II. ዳዊት በምድር ላይ ላለው ለእግዚአብሔር ማደሪያ፣ ለእግዚአብሔር ታቦት ማደሪያ ግድ ተሰኘ—2 ሳሙ. 6፡1—7፡29፤ መዝ. 132፡1-18፦**

ሀ. ምንም እንኳን እግዚአብሔር ዳዊት መቅደሱን እንዲገነባ ባይፈልግም፣ ገንቢውን፣ የግንባታ ስፍራውን፣ እና መቅደሱን የመገንቢያ ቁሳቁሶችን አዘጋጀ፤ በተጨማሪም እግዚአብሔር በመንፈሱ ለዳዊት የመቅደሱን ንድፍ ገለጠለት፣ ዳዊት ከመሞቱ በፊትም ይህንን ንድፍ ለልጁ ለሰሎሞን ሰጠው፤ ስለዚህ ዳዊት ለመቅደሱ ግንባታ መጠናቀቅ አገልግሎቱን ፈጸመ፣ ከእግዚአብሔርም ጋር አብሮ ሠራ—2 ሳሙ. 8፡11፤ 1 ነገ 7፡51፤ 1 ዜና. 22፡14-16፤ 29፡1-5፤ 28፡11-19፤ ሐዋ. 13፡22፣ 36።

ለ. ዳዊት የእግዚአብሔርን መቅደስ ለመገንባት ቀንቶ ነበር (2 ሳሙ. 7፡13 )፣ እግዚአብሔር ግን የዳዊትን መልካም ውጥን አልተቀበለውም፤ እግዚአብሔር "እኔ የማድርበትን ቤት የምትሠራልኝ አንተ ነህን?" ብሎ እንዲጠይቀው ነቢዩ ናታንን ወደ ዳዊት ላከው—ቁ. 5፦

1. ይህ የሚሳየው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለን ሥራችን እና አገልግሎታችን ሁሉ በእግዚአብሔር የተነሳሳ መሆን እንዳለበት እና በመሻቱ መሠረት መሆን እንዳለበት ነው፤ በሰው የተነሳሳ ወይም የተጀመረ ነገር ሁሉ፣ ምንም ያህል ለእግዚአብሔር የሆነ ቢሆንም እንኳን፣ የክርስቶስ መገኘት የሌለው ኃይማኖታዊ ድርጊት ነው።
2. እግዚአብሔርን ለማገልገል ያለን ልብ ተቀባነት አለው፣ ለእርሱ የሆነ ነገርን የምናደርገው ውሳኔ ግን ተቀባይነት የለውም፤ እግዚአብሔር ለዳዊት ".. አንተ ነህን" አለው፤ እግዚአብሔር በእርሱ ቦታ ማንኛውንም ነገር እንድንወስን አይፈልግም።

ሐ. ዳዊት እግዚአብሔርን የሚፈራ እና ከእግዚአብሔር ጋር የተባበረ ሰው በመሆኑ ምክንያት፣ እግዚአብሔር በናታን በኩል መቅደሱን የሚገነባው ለመሆን ያለውን ቁርጠኛነት እንዲያቆም ሲነግረው ምላሽ አልሰጠም፤ ዳዊት መቅደሱን የመገንባት መሻቱን ከመከወን መቆሙ ታላቅ ጉዳይ ነው፤ እህት ኤም.ኢ. ባርበር እንዲህ አለች፣ "ለእግዚአብሔር ሲል መሥራቱን ማቆም የማይችል ሰው ለእግዚአብሔር መሥራት አይችልም" (*The collected works of Witness Lee, 1953,* vol. 1, "Knowing Life and the Church" ከሚለው መጽሐፍ ከገጽ 283 የተወሰደ)—ሉቃ. 10፡38-42።

መ. የዳዊት ማቆም በአጽናፍ-ዓለም ውስጥ ሁለት እጥፍ ምስክርነትን መሥርቷል፦ አንደኛ፣ በአጽናፍ-ዓለም ያለው ሥራ ሁሉ ከእግዚአብሔር እንጂ ከሰው መምጣት የለበትም፤ ሁለተኛ፣ የሚያስፈልገው ነገር እግዚአብሔር ለሰው የሚያደርገው ነገር እንጂ ሰው ለእግዚአብሔር የሚያደርገው አይደለም—2 ሳሙ. 7፡11-14፣ 18፣ 25።

ሠ. እግዚአብሔር የሚፈልገው ትብብራችንን ብቻ እንደሆነ ከውስጥ ጥልቀታችን መማር አለብን፤ ለእርሱ ምንም ነገር እንድናደርግ አይፈልግም፣ አመለካከቶቻችንን፣ ውሳኔዎቻችንን፣ ሀሳቦቻችንን በሙሉ ማቆም አለብን፤ እርሱ እንዲናገር፣ ወደ ውስጥ እንዲመጣ እና እንዲያዝ ልንፈቅድለት ይገባል—ማቴ. 17፡5።

**III. እግዚአብሔር በዳዊት ላይ ያደረገው የቅጣት ፍርድ ዘገባ ዛሬ ለእኛ እንደ ማስጠንቀቂያ ተጽፎልናል (1 ቆሮ. 10፡11)፤ እግዚአብሔር አፍቃሪ እና መሀሪ ብቻ ሳይሆን ፍትሃዊ እና የሚፈራም ጭምር ነው፤ እግዚአብሔር ዳዊትን ይቅር ብሎታል፣ ነገር ግን በአገዛዛዊው ጽድቁ መሠረት ቀጥቶታል (2 ሳሙ. 12፡10-14)፡-**

ሀ. የእስራኤል ጠላቶች ሁሉ ከተገዙ በኋላ እና ዳዊት እንደ እስራኤል ንጉሥ ከፍ ከፍ ካለ በኋላ፣ ሰላማዊ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ሳለ ታላላቅ ኃጢአቶችን ሠራ—ምንዝርና እና ነፍስ ማጥፋት፤ ይህ የሚያሳየው ሰላማዊ በሆነ ሁኔታ የተመቻቸን በምንሆንበት ጊዜ ሁሉ፣ የሥጋችንን ምኞት ለመፈጸም እንደምንታለል ነው—11፡1-27፤ 1 ጴጥ. 4፡1 እና የግርጌ ማስታወሻ 4።

ለ. የዳዊት ኃጢአት የዓይን አምሮቱን እና የሥጋ ምኞቱን ለማርካት የመፈለጉ ውጤት ነበር (2 ሳሙ. 11፡2-3) ፤ ዳዊት የንግሥናውን ኃይል በመጠቀም (ቁ. 4-5)፣ (የሰውን ሚስት) በመቀማት በፈቃዱ አመነዘረ።

ሐ. እንዲህ ያለውን ድርጊት ከፈጸመ በኋላ፣ ዳዊት ክፉ ድርጊቱን በማስመሰል ለመሸፈን ሞከረ (ቁ. 6-13)፤ ከዚያም የኦሪዮንን ሚስት ለመውሰድ ከኢዮአብ ጋር በማሴር ታማኝ አገልጋዩን ኦሪዮንን ገደለው (ቁ. 14-25፤ 12፡9)።

መ. በዚህ አንድ ኃጢአቱ ዳዊት የአሥርቱን ትእዛዛት የመጨረሻዎቹን አምስቱን አፈረሰ (ዘጸ. 20፡13-17)፤ ኃጢአቱ ለእግዚአብሔር ታላቅ ስድብ እና በደል ነበር፣ ከዚያ በፊት የተቀዳጃቸውን ስኬቶችንም ሁሉ ለጥቂት አሳጥቶት ነበር።

ሠ. ዳዊት በእግዚአብሔር ልብ መሠረት የሆነ ሰው በመሆኑ (1 ሳሙ. 13፡14) ለሚመጣው ክርስቶሱ በምድር ላይ መንግሥቱን ለመመሥረት የንግሥናው ዘመን እንዲጀመር ለእግዚአብሔር መንገድ የሰጠ ነበር፣ የሥጋን ምኞት በማርካት ጉዳይ ግን ወድቋል (1 ነገ. 15፡5)፤ በዚህ ጉዳይ ዳዊት ልቅ ነበር፣ በመንፈሳዊ ፍለጋው እግዚአብሔርን በመከታተሉ የደረሰባቸውን ከፍተኛ ስኬቶች መሥዋዕት አድርጓል፤ ይህ ለእኛ ለሁላችን ማስጠንቀቂያ ሊሆንልን ይገባል።

ረ. ዳዊት ክፉው በሚፈትንበት ወሳኝ ጊዜ በሥጋዊ ምኞቱ ላይ ጠንክሮ በመግዛት ፋንታ በሥጋው ምኞት በመዘፈቅ እግዚአብሔርን ፈጽሞ ያስቆጣ ከባድ ኃጢአት መፈጸሙ ምንኛ የሚያስቆጭ ነው።

ሰ. እግዚአብሔር ዳዊትን ይወደው ነበር፣ ነገር ግን በኃጢአቱ ምክንያት እርሱም ከአሥራሁለቱ ነገዶች አሥራ-አንዱም ክብራቸውንና እና ስፍራቸውን አጡ (2 ሳሙ. 20፡1-2)፤ የዳዊት ኃጢአት በእግዚአብሔር የተሰጠውን መንግሥት መከፋፈል ያመጣውን (1 ነገ. 11፡9-13፤ 12፡1-17) የሰሎሞንን የመበላሸት ዘር (12፡24) እና በስተመጨረሻ የአገሪቱን መጥፋትን እና የአባቶቻቸውን ቅድስት ምድር ማጣትን፣ የቅዱሱ ሕዝብ በግዞት መማረክን፣ እና በምድር ሁሉ ላይ መበተንን እና እስከዛሬ ድረስ ሰላም ማጣት ያስከተለውን በንግሥና ውስጥ የሰሎሞን ዘሮችን መበላሸትን ዘር ዘራ።

ሸ. ከዳዊት ታሪክ የእግዚአብሔር አገዛዛዊ እጅ ሥር መውደቅ ከባድ ጉዳይ እንደሆነ ማየት እንችላለን (2 ሳሙ. 12፡10-14)፤ ዳዊት ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ኅብረት በጣም በፍጥነት መለሰ፣ የእግዚአብሔር ቅጣት ግን እርሱ ከሞተ በኋላም እንኳን ቀጠለ (ቁ. 15—20፡26)።

ቀ. በመዝሙር 51 ላይ እንደተገለጠው ኃጢአቶቹን በመናዘዝ በኩል ዳዊት ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው ኅብረት ተመለሰ፣ ነገር ግን የእግዚአብሔር አገዛዛዊ እጅ ሥር ወደቀ፤ ከውድቀቱ በኋላ ዝሙት፣ ግድያ እና አመጽን ጨምሮ በቤተሰቡ መካከል ብዙ ክፋቶች ተከሰቱ—2 ሳሙ. 12፡15—20፡26።

በ. እግዚአብሔር ዳዊት ላይ ከባድ ቅጣት የፈፀመበት ምክንያት ኃጢአቱ እጅግ ክፉ ስለነበር ነው፤ በዳዊት ቤተሰብ ውስጥ የሆነው ሆኖ የማያውቅ ክፋት ምንጩ ዳዊት የሥጋውን ምኞቱ ለማርካት መፈለጉ ነበር፤ ይህ የሚያሳየው እርሱን በሚወዱት ላይ የእግዚአብሔር ቅጣትና አገዛዛዊ ማረቁ ልጆቻቸው ላይ ሳይቀር ተፅእኖ ሊኖረው እንደሚችል ነው።

ተ. ይህ ለእኛ ከክርስቶስ ጋር ባለን ግንኙነት እውነተኛ ማንቂያ እና ማስጠንቀቂያ ሊሆን ይገባል፤ እኛ የሆንነው፣ የምንፈልገው፣ ለማድረግ የወጠንነው እና ምልልሳችን በክርስቶስ ውስጥ ከመቀየታችን እና ለድሰታችን ፍለጋ በሌለው የክርስቶስ ብልጥግናዎች ሁሉ ውስጥ ከመሳተፋችን ጋር በጣም ይገናኛል፤ በእነዚህ ጉዳዮች ከእግዚአብሔር ጋር ትክክል ካልሆንን፣ ክርስቶስን እንደ ድሰታችን እናጣዋለን።

ቸ. ከእርሱ ጋር በተገናኘ ተገቢ ካልሆንን፣ ለድሰታችን እንደ ማደሪያ ስፍራችን፣ ሁሉን እንዳካተተው መልካሙ ምድራችንና ለድሰታችን እንደሚያስፈልገን ሁሉ ነገራችን ሁሉን-ያካተተው ክርስቶስ ከውስጡ ይተፋናል እና ከዚያም ወዲያ እርሱን እንድንደሰተው አይፈቅድልንም—ዘሌ. 18፡25፤ ራእ. 3፡16።

ኀ. በመጨረሻም ዳዊት ማርጀት ብቻ ሳይሆን እየደበዘዘም ሄደ፤ የዳዊት ሕይወት እንደ ደማቅ ፀሐይ መውጣት መልካም ጅማሬ ነበረው እና ሕይወቱ ከሥራው ጋር በቀትር ደምቆ እንደሚያበራ ፀሐይ ሆነ፤ ነገር ግን የሥጋ ምኞትን ለማርካት በመፈለጉ (2 ሳሙ. 11፡1-27) ሥራውን አበላሸው፣ ብሩህ የነበረውን ሕይወቱንም እንደ ምሽት ጀንበር እንዲደበዝዝ

አደረገው፤ በዳዊት የሽምግልና እድሜ ብሩህ፣ የላቀ ወይም ግርማዊ የሆነ ነገር አልነበረም (1 ነገ. 1:1-4፤ ተዛ. ዘዳ. 34:7፤ ዘፍ. 48:14-16፤ ምሳ. 4:18)።

ነ. የክርስቲያን ሕይወት የእግዚአብሔርን አገዛዝ የመማር ህይወት ነው፤ የዘራነውን እናጭዳለን፤ ለሌሎች ይበልጥ ሊጋስ ስንሆን፣ እግዚአብሔር ለእኛ ይበልጥ ለጋስ ይሆናል፤ ለወንድሞቻችን ክፉና ጨካኝ ከሆንን፣ እግዚአብሔር ለእኛም ክፉና ጨካኝ ይሆንብናል፤ ሌሎች ሲታመሙ ወይም ችግር ውስጥ ሲገቡ፣ እነርሱን የምንረዳበት እንጂ እነርሱን የምንነቅፍበት ጊዜ አይደለም—ገላ. 6:7፤ 1 ተሰ. 5:14-15፤ ሉቃ. 6:36-38፤ ማቴ. 7:1-2፦

1. ለጋስና ይቅር ባይ ሰዎች መሆንን መማር አለብን፤ ሌሎች ላይ ጨካኝ ከሆንን፣ እግዚአብሔርም እኛ ላይ ጨካኝ ይሆናል፤ መንቀፍ፣ መኰነን እና ስለ ሌሎች ቀላል በሆነ መንገድ መናገርን ማስወገድ አለብን፤ ስለ ሌሎች ያለን ነቀፋና ግድየለሽ አስተያየቶቻችን ብዙውን ጊዜ ራሳችን ላይ ፍርድ ይሆናሉ—6:15፤ 18:23-25።
2. ለአንድ ምክንያት ብቻ በአሳዛኝ መንገድ የወደቁ ብዙ ወንድሞች አሉ—ቀደም ሲል ሌሎችን ክፉኛ በሆነ መንገድ ተችተዋል እና ዛሬ ያላቸው ብዙዎቹ ድክመቶቻቸው በፊት የተቿቸው እነዚሁ ድክመቶች ናቸው።
3. እኛ የተጠራነው ሌሎችን ለመባረክ ነው፣ ስለዚህ እንደተባረኩ ሰዎች በረከትን እንድንወርስ ሁልጊዜ ሌሎችን መባረክ አለብን፤ ሌሎችን የምንባርክበትን ነገር እኛ ራሳችን እንወርሰዋለን—1 ጴጥ. 3:8-11፤ ማቴ. 10:13፤ ተዛ. ዘኍ. 6:22-27።

© 2021 Living Stream Ministry